**አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች የቤተሰብ ህይወት ትምህርት ላይ የወላጆች በምርጫ የማስተማር ፎረም - 4ኛ ክፍል**

የተማሪው ስም : ______________________________ስልክ ቁጥር: __________________
የአስተማሪው ስም: ______________________________ቀን: _____________________

እኔ እዚህ ያለሁት ከተዘረዘሩት አላማዎች ውስጥ ልጄ እንዳይሳተፍ የምፈልግበትን ምርጫ እንዳደርግ ነው። ልጄ እንዳይሳተፍ በማደርግባቸው አላማዎች ላይ፣ ልጄ ያለምንም ተፅእኖ አማራጭ አሳይመንቶች እንደሚሰጡት ተረድቻለሁ። ልጄ አሳይመንት በሚሰራበት እና ለአሳይመንቱ ውጤት በሚሰጥበት ወቅት፣ በትምህርት ቤቱ ህጎች እና ፖሊሲዎች መመራት እንደሚጠበቅበት ተረድቻለሁ።

**<u>አቅጣጫዎች</u>:** እባክዎ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አላማዎች ላይ ልጅዎ እንዳይሳተፍበት የሚፈልጉትን ነገር ካለ ምልክት ያድርጉበት።

___ **4.1 ተማሪው የሰዎችን የመራቢያ አካላትን መለየት ይችላል።**
<u>መግለጫ</u>: ትኩረት ከሚደረግባቸው በታዎች ውስጠ የወንዶች የመራቢያ አካትላት፡ የወንድ ብልት፣ ቴስቲክልስ፣ ስክሮተም እና አርቴራ ሲሆኑ የሴቶች የመራቢያ አካላት ደግሞ፡ ማህፀን፣ ኦቫሪ፣ የሴት ብልት እና ፋሎፒያን ትዩብ ናቸው።

___ **4.2 ተማሪው በጉልምስና ወቅት የሚከሰቱ የአካል ለውጦችን መለየት**
<u>መግለጫ</u>: ሰዎች በሚያድጉበት ግዜ በግላቸው ወንዶች እና ሴቶች የሚኖራቸው ወሲባዊ ለውጦችን ይቀርቡላቸዋል። ከወንዶች ባህሪዎች ውስጥ፡ የትከሻ መስፋት፣ የእጅ እና እና እግር መርዘም፣ የሰዎችን እድገት በሆርሞኖች በኩል ስለሚቆጣጠረው ፒቱተሪ ግላንድ፣ መራቢያ አካላት ዙሪያ እና ብብት ስር ስለሚበቅሉ ፀጉሮች እና የድምፅ ለውጦች ከሚቀርቡት መካከል ናቸው። ከሴቶች ባህሪያት ደግሞ፡ ዳሌ አካባቢ መስፋት፣ የጡት ማደግ፣ የእድገት ሆርሞንን ስለሚቆጣጠረው ፒቱተሪ ግላንድ፣ የመራቢያ አካላት ዙሪያ እና ብብት ስር ስለሚበቅለው ፀጉር እና ስለወር አበባ ኡደት ከሚጠቀሱት ውስጥ ናቸው። እነዚህ ወሲባዊ ለውጦች እና እድገቶች ከሰው ሰው እንደሚለያይ እና ተፈጥሮአዊ እና ምንም ችግር የሌለው እንደሆነ አትኩሮት የሚሰጥበት ጉዳይ ነው። ተማሪዎች እድገታቸው ከእኩያቸው የፈጠነ ወይም የዘገየ ከሆነ ጭንቀት እንዳያድርባቸው በግላቸው እርዳታ ይደረግላቸዋል። የወሲብ ተግባርን የማዘግየት ጥቅም እና ልጅን ዘግይቶ የመውለድ ጥቅም ይብራራሉ። በተጨማሪም ከእነዚህ የሰውነት ለውጦች ጋር ተያይዞም የሰውነትን ንፅህናን የመጠበቅ አስፈላጊነት ይነገራቸዋል።ችግሮች ሲከሰቱ፣ ችግሮችን ለመፍታት አስተማሪዎች እና ወላጆች በጋራ መስራታቸውን እንዲቀጥሉ ይበረታታሉ።

___ **4.3 ተማሪው ስለሰው አፈጣጠር እና ስለፅንስ እድገት እንዴት እንደሆነ እውቀት እንዲያገኙ ይደረጋል።**
<u>መግለጫ</u>: መመሪያው ስፐርም እና እንቁላል ሲገናኙ እና ማህፀን ውስጥ እንዴት ፅንስ እንደሚፈጠር የሚያስረዳ ነው።

___ **4.4 ተማሪው ዋና ዋና የሚባሉ የሰው ልጅ ስሜቶች ምን እንደሆኑ እና ተገቢ የሆኑ ማስተናገጃ መንገዶች ምን እንደሆኑ እንዲያውቁ ይደረጋል።**
<u>መግለጫ</u>: ጠንካራ የሆኑ ስሜቶችን በጎም ይሁኑ መጥፎ እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው መረዳት እንዲችሉ ትኩረት ይደረጋል። ተማሪዎች ደስታን እና የተነቃቃ መንፈስን እና ከማጣት፣ ከመገፋት፣ ከፍቺ፣

ከሞት፣ ከህመን እና ከለውጥ ጋር ተያይዘው የመከሰቱ ስሜቶችን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ይማራሉ። ተማሪዎች ለእንደዚህ አይነት ስሜቶች ምን አይነት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው እና አዎንታዊ ጤናማ የአእምሮ ልምምዶችን በመጠቀም ስሜትን ከሚጎዱ ነገሮች እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉ ይማራሉ።

___ **4.5 ተማሪው ያለውን ጠንካራ እና ደካማ ጎን እንዲያውቅ እና እንዲቀበለው ይደረጋል።**
<u>መግለጫ</u>: ለስኬታማነት እና ለውድቀት ሃላፊነትን መውሰድ፣ በስኬት ወቅት መኩራት እና ስህተቶች ለቀጣዩ ስኬት በጎ የሆነ ትምህርት እንዳላቸው መረዳት ከሚጠቀሱት ውስጥ ናቸው።

___ **4.6 ተማሪው በቤተሰብ ውስጥ ሀላፊነትን የመውሰድ አስፈላጊነትን እና እንደቤተሰብ አባል ስኬታማ ተሳትፎ የማድረግን ጥቅም ይረዳል።**
<u>መግለጫ</u>: ትኩረቱ በቤተሰብ ውስጥ ስራን መከፋፈል፣ ማገዝ፣ መደገፍ እና ከቤተሰብ አባላት ጋር ንግግርን ማድረግ ከሚጠቀሱት ውስጠ ናቸው። የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ላለባቸው የቤተሰብ አባላት አስፈላጊው እገዛ ይደረግላቸዋል።

___ **4.7 ተማሪው በልጆች ላይ ስላሉ ብዝበዛዎች እና ቸልተኝነት ምክናቶች እንዲገልፅ ድረጋል።**
<u>መግለጫ</u>: የልጆች ብዝበዛ እና ቸልተኝነት የቃሉ ትርጉም ምን እንደሆነ ይብራራል (ወሲባዊ ብዝበዛን እና የኤሌክትሮኒክ ትንኮሳንም ያጠቃልል) እና በተጨማሪም ራሳቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ እና ለሚያምኗቸው ትላልቅ ሰዎች ልክ እንደ ወላጅ፣ አስተማሪ፣ ሚኒስቴር፣ አያቶች ወይም አሳደጊዎች ያሉ ሰዎች የመናገር ጥቅሞች ይገለፅላቸዋል።

___ **4.8 ተማሪው አደንዛዥ እፅ ለመጠቀም የሚያበቁ ምክንያቶችን ይለያል።**
<u>መግለጫ</u>: አልኮል፣ ሲጋራ እና ሌሎች እፆችን ለመጠቀም የሚያነሳሱ ምክንያቶች ምን እንደሆኑ ልክ እንደ 'የማደግ ምልክት'፣ 'በእኩዮች ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት'፣ በግዜያዊነት በሚጀምሩ እፆች ምክንያት ወይም ከስሜት ጉዳት ለመገላገል የሚወሰዱ እፆች ላይ ውይይት ይደረጋል። የአንድ ሰው ፍላጎት እና ስሜት ከእፆች ወይም ሌሎች መሳሪያዎችን ከመጠቀም ታቅቦ እንዴት ሁኔታዎችን ማስተናገድ እንደሚችል ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል።

___ **4.9 ተማሪው አንዳንድ እቃዎች የመጠቀም እና አላግባብ የመጠቀምን ጉዳት ይገነዘባል።**
<u>መግለጫ</u>: ትኩረቱ ሲጋራን፣ አልኮልን እና ሌሎች እፆችን አግባብ ባልሆነ መንገድ መጠቀም ላይ ነው።በውስጡም የሚይዘው እቃዎች ያለአግባብ መጠቀም በግለሰቡ ላይ እና በሌሎች ላይ ልክ እንደ ቤተሰብ ላይ ስለሚደርስ ጉዳት፣ ወሲባዊ ትንኮሳ እና የልጆች ጥቃትን የሚመስሉ ጉዳቶችን እንደሚያደርስ የሚያስረዳ ነው።

**ትምህርት ቤታችሁ በወሰነው ቀን መሰረት ይህንን ቅፅ በመሙላት ለርእሰ-መምህሩ እባክዎን ያስረክቡ**

የወላጅ/የአሳዳጊ ፊርማ: ________________________________________ ቀን: __________